# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ጠጠር ወርዋሪ እጆች!!

ፍስሐ ጌታቸው

የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ከጥገኝነት ተላቆ በራስ አቅም በመከወን ወጪን መቀነስ መንግሥት የሚከተለው አንዱ አቅጣጫ ነው። ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ላይ የሚያጋጥሙ ድንገተኛ ብልሽቶችን በራሱ የሰው ኃይል በመጠገን ወጪን የማዳን አቅም እየፈጠረ መጥቷል።

እንደምን ሰነበታችሁ ውድ አንባቢያን! ባለፈው ሳምንት ዕትማችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከውሃ፣ ከንፋስ፣ ከከርሰ-ምድር እንፋሎትና ከደረቅ ቆሻሻ ኃይልን በማመንጨት የተጣለበትን አገራዊ ተልዕኮ ለመወጣት እያከናወነ ያለውን ሥራ ማስነበባችን ይታወሳል።

በዛሬው ዕትማችን ደግሞ አገሪቱ ለተለመቻቸው በርካታ የልማት ግቦች ስኬት በቂና አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ በኩል ተቋሙ እያከናወነ ያለውን የጥገና ሥራ ለመቃኘት እንሞክራለን። ተቋሙ ከአዳዲስ የኃይል ማመንጫ ግንባታዎች በተጨማሪ በሥራ ላይ ያሉ ነባር ኃይል ማመንጫዎችን በሙሉ አቅማቸው እንዲሠሩ ከሚያደርግበት በርካታ ተግባራት መካከል አንዱ በራስ አቅም እየተከናወኑ ያሉ የጥገና ሥራዎች ይጠቀሳሉ።

ለዚህ ርዕሰ ጉዳይ አስረጂ የሚሆነን በ2002 ዓ.ም ተመርቆ በይፋ ሥራ በጀመረው በጊቤ ሁለት ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የተከናወነው የጥገና ሥራ ሲሆን በሥራው የተሳተፉትንና ለአገራዊ ዕድገት ስኬት የበኩላቸውን ጠጠር ሲወረውሩ የተመለከትናቸው እጆችን ልናስቃኛችሁ ወደድን። መልካም ንባብ !

420 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለው የጊቤ ሁለት ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ከአዲስ አበባ በ250 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በየም ልዩ ወረዳ የሚገኝ ነው። የጊቤ ሁለት ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ኃይል እንዲያመነጭ የሚያስችለውን ውኃ የሚያገኘው 184 ሜጋ ዋት አመንጭቶ ከሚወጣው ከጊቤ አንድ ውኃ ነው። ውኃው ከጊቤ አንድ ኃይል አመንጭቶ እንደወጣ በቅርብ ርቀት በተሠራው መለስተኛ ግድብ እንደገና እንዲያዝ ከተደረገ በኋላ ወደ ጊቤ ሁለት በመሬት ውስጥ በሚያልፍ ዋሻ (underground tunnel) አማካኝነት ይሄዳል።

ዋሻው 26 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና ሦስት ነጥብ ስድስት ሜትር ዲያሜትር ስፋት አለው። ውኃው ከብረት በተሠሩ አንድ ነጥብ ሶስት ኪሎ ሜትር ርዝመትና ሁለት ነጥብ አንድ ሜትር ዳያሜትር ስፋት ባላቸው ሁለት አሸንዳዎች (Penstock) ከተጓዘ በኋላ እያንዳንዱ አሸንዳ እንደገና ለሁለት ተከፍሎ ወደ አራቱም ዩኒቶች በመሄድ ኃይል ያመነጫል።

ጣቢያው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት አንደኛው ዩኒቱ ሙሉ ለሙሉ ሥራ ሲያቆም ሌላኛው ደግሞ ኃይል ማምረት ከሚጠበቅበት 1/4ኛውን ብቻ በማምረቱ በሙሉ አቅሙ እንዳያመርት እንቅፋት ተፈጥሮበት ከርሟል። ታዲያ የተፈጠረውን ችግር በራስ አቅም ለመቅረፍ የተደረገውን ጥረት ውጤታማ ማድረጉ አስገራሚና አስደማሚ ከመሆን አልፎ ተስፋ ሰጪ ሆኗል። አገር በቀል እጆችን በመጠቀም ተቋሙን ወደተሻለ ደረጃ ማሻገር እንደሚቻልም አመላክቷል።

የጣቢያው ሠራተኞች በዩኒቶቹ ላይ ያጋጠመውን ችግር ዓይነትና ስፋት በመለየት ጥገናውን በራስ አቅም ማከናወን እንዲቻል ለተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ማሳወቃቸውንና ፈቃድ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን፣ የተቋሙ የበላይ አመራርም ለጥያቄው ይሁንታ መስጠቱ ለቡድኑ ተነሳሽነትን በመጨመሩ ምክንያት ወደ ጥገና ሥራ መግባቱን ያስታውሳሉ።

በወቅቱ ዩኒቶቹ አገልግሎት እንዳይሰጡ ያደረጋቸው ችግር የፖወር ኖዝል ብልሽት እንደነበር የሚናገሩት ባለሙያዎቹ፤ ፖወር ኖዝል የመርፌ ቅርጽ ያለው (needle valve) ሲሆን ዩኒቶቹ እንደመጨን አቅማቸው ውኃን ለመመጠን የሚያገለግል መቆጣጠሪያ አካል ነው። ችግሩ ተለይቶ ወደ ጥገና ሥራ ከመገባቱ በፊት ለጥገና ሥራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ ሰነዶችን፣ ባለሙያዎችን፣ የጥገና መሳሪያዎችንና ግብዓቶችን የማሰባሰብ ሥራ ተሠርቷል።

የፖውር ኖዝል ችግርን ለማስተካከል የተበሉ ሲሎችን ለማስተካከል ፓወር ኖዝሎችን ማውረድና መፍታት የግድ በመሆኑ እያንዳንዳቸውም ስድስት ሺ ኪሎ ግራም የመመዘን ክብደት ያላቸው ስድስት ፓወር ኖዝሎችን ከዩኒት አንድ ላይ መፍታት አስፈልጓል። ፓወር ኖዝሎቹን በሰው ኃይልና በማሽነሪዎች በመታገዝ በማውረድ፣ የመፈታት፣ የማፅዳት እና የመቀየር እንዲሁም ሞደፊክ ሠርቶ መልሶ የመግጠም ሥራ እንደተሠራ የጥገና ቡድኑ አባላት ይገልፃሉ።

ከፖወር ኖዝል ጥገና ጎን ለጎን Main inlet valve (MIV servomotor) መሳሪያዎች ጥገና ተከናውኗል። MIV servomotor ወደ ተርባይን የሚገባውን የውኃ መጠን ለመቆጣጠር የሚያገለግል ቁስ ሲሆን በመዝጊያው በኩል የዘይት መፍሰስ ችግር በማጋጠሙ በዩኒት አንድ ላይ ሁለት እንዲሁም በዩኒት ሦስት ላይ አንድ በድምሩ ሦስት (MIV servomotor) የጥገና ሥራዎች ተከናውነዋል።

በዚህም ሙሉ በሙሉ ማመንጨት አቁሞ የነበረውን የዩኒት አንድ የመጨን አቅም ወደ 105 ሜጋ ዋት እንዲሁም 25 ሜጋ ዋት ብቻ ይጭን የነበረውን ዩኒት ሦስት 100 ሜጋ ዋት ኃይል እንዲያመነጭ በመደረጉ ጣቢያው 180 ተጨማሪ ኃይል እንዲያመነጭ አድርገዋል። በቀጣይም ይህን መሠል ሥራዎችን በዩኒት ሁለትና አራት ላይ ለመሥራት ዕቅድ መያዙን ለመረዳት ችለናል።

በጣቢያው ከተሠሩ ሥራዎች መካከል ሌላው የኃይል ጭነትን ለማስተካከል የሚረዳውን የርቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ማዘመን ነው። ይህም ለረጅም ጊዜ በማኑዋል ይሠራ የነበረውን የኃይል ጭነት በማስተካከል በቀላሉ ከኃይል ማመንጫ ቤት ሆኖ መቆጣጠር ማስቻሉ ከባድ የነበረውን ሥራ ቀላል እንዲሆን አድርጎታል።

በተጨማሪም ማሽኑ ያለበትን ችግር በድምፅ ለመለየት የሚያስችል የድምፅ መቅጃ (sound recorder) ተገጥሞ በመሥራት ላይ እንደሆነም አንስተውልናል። በተመሳሳይ መልኩ በምስራቅ አፍሪካ የጀርመን ተራድኦ ድርጅት ድጋፍ Voith በተባለው ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የጥገና ማኔጀመንት ስርዓት (maintenance management system) ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የጥገና ቡድኑ አባላት ነግረውናል።

የተቋሙ ማኔጅመንት አባላት እና የኃይል ማመንጫዎች ኦፕሬሽን ጽሕፈት ቤት አመራሮች በተቋሙ ሠራተኞች ላይ ከፍተኛ እምነት አሳድረው ጥገናው እንዲከናወን ፈቃድ መስጠታቸው እና በየጊዜው አስፈላጊ ድጋፎችን ማድረጋቸው ለውጤታማነታቸው አቅም እንደፈጠረላቸው የተናገሩት ባለሙያዎቹ፤ የተቋሙ አመራሮች ስላሳደሩባቸው አመኔታና ስላደረጉላቸው ድጋፍም ልባዊ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

እኛም እንዲህ ዓይነቱ አሠራር የሙያተኛውን ብቃት ከማሳደግና የተቋሙን ወጪ ከማዳን አንጻር ጠቀሜታው ከፍ ያለ በመሆኑ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እየተመኘን ተሰናበትን።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ